ከዚህ በፊት በሕገ-ወጥ መልኩ እንዳልተጓጓዙ እርግጠኛ ሆነው አሁን ግን ምናልባት ያሉበትን ቦታ ለማንም ሳይናገሩ ለመልቀቅ እያቀዱ ይሆናል። ይህ ከሆነ፤ ከመሄድ በፊት፤ በዚህ በራሪ ወረቀት ላይ ያለውን ስልክ ቁጥር በስልኩዎ ላይ በመጻፍ እና በትንሽ ብጣሽ ወረቀት ላይ መዝግበው በቦርሳዎ ውስጥ አንድ ቦታ በመደበቅ ይያዙ። ከቻሉ በቃሉዎ ለማስታወስ ይሞክሩ እናም ወደፊት በሕገ-ወጥ መልኩ እንደተጓጓዙ ከተረዱ ወይም ነገሮች ተሰፋ እንዳደረጉት ሆነው ካላገኙ ይደውሉ። ወደፊት በየትኛውም ሰዓት ደህንነት ካልተሰማዎት ወደ ሂልግደን ተመልሰው መምጠት ይችላሉ።



**NSPCC**

**0800 107 7057**



***If a young person points to this section of this leaflet they are indicating to you that they may have been trafficked into the UK and need your help now. Please ring the above number for advice.***

# የሕፃናት ሕገ-ወጥ ንግድ




## የችግሩ ተጎጂ ኖት?

ምናልባት ለሰዎች ጥቅም (ንግድ) በሕገ-ወጥ መንገድ ወደ ዩኬ ተጎጉዘው መጥተው ሊሆኑ ለሚችሉ ወጣቶች የሚሆን መመሪያ

## ለምን ይህ በራሪ ወረቀት አሁን ተሰጠት?





ምናልባት እርሶን ሰዎች ወደ ዩኬ ያመጡዎት ጉልበቱዎን ሊመዘብሩ ሊጨቁኑዎት ሊሆን ይችላል። ይህም የሕፃናት ሕገ-ወጥ ንግድ ይባላል። ይህንንም የምናስብበት ምክንያት ወጣት ልጆች ተገደው ወደ ሴተኛ አዳሪነት እና

በቡና ቤቶችና በምግብ ማብሰያ ቤቶች ውስጥ ያለ ምንም ክፊያ ወይም በጣም ትንሽ በሆነ ገንዘብ ተገደው እንደ ገቡ ስለነገሩን ነው። ጥሩ ሥራ እንደሚሰሩ ቃል ተገብቶሎት ነበር? ጥሩ ትምህርት? የመኖሪያ ቦታ? እነኚ ነገሮች ውሸት የሆኑ እንደሆነ ያስቡ። አሁን የሉበትን ሰላማዊ ሁኔታ ትተው የማያውቁትን ሰዎች እንዲገናኙ ተነግሮት ከሆነ አንድ ጊዜ ቆም ብለው ምን ሊደርስቦት እንደሚችል ያስቡ።.



እኛ እዚህ ያለነው ሊንረዳዎት ነው‌ና ሀሳብ ስለሆነቦት ነገር ሁሉ ሰራተኞቻችን ቢያማክሩ ምንም ችግር ውስጥ አይገቡም። እባኳዎን ይህንን አሁኑኑ ችግር ውስጥ ከመግባቶ በፊት ያድርጉ።



እንግሊዘኛ መናገር የማይችሉ ከሆኑ እባኳዎን በዚህ በራሪ ወረቀት ጀርባ ያለውን የእንግሊዘኛ ትርጉም ለአንድ ሰው ይጠቁሙ።